የኢትዮጵያ ግብርና
ባለስልጣን

Ethiopian Agricultural
Authority

# ዜና መፅሔት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

**ቅጽ 1 ቁጥር 62** **ታህሳስ 2016ዓ.ም**

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፦ ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

የፌስቡክ ገጻችን፡- Ethiopian Agri cultural Authority

የቴሌግራም ገጻችን፡- eaa_123

ዌብሳይት፡- www.eaa.gov.et

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ሁለተኛ ዙር የአቅም ግንባታ ስልጠና ለፈፃሚዎች ሰጠ።







የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በአዋጅ የተሰጠዉን ስልጣንና ተግባር በብቃት በመፈፀም በተለይም በግብርናው ዘርፍ የተጠናከረ ሬጉላቶሪ ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር እየሰራ ሲሆን በዚህም መሰረት በአለም አቀፉ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ የባለሙያዎችን አቅም በተለያዩ መንገዶች መገንባት ቅድሚያ የሚሰጠዉ ተግባር በመሆኑ በስሩ ለሚገኙ ፈፃሚ ባለሙያዎች ከታህሳስ 25/2016 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ ሁለት ቀናት በአዳማ ከተማ በኤፋታህ ሆቴል ሁለተኛዉን ዙር የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል ፡፡

የስልጠና መድረኩን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእፅዋት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዳለ ሀብታሙ ሲሆኑ የስልጠናው ዋና አላማ ባለስልጣን መስሪያቤቱ በአዲስ የተደራጀ እና እየተገነባ ያለ ተቋም እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ያሉ አመራሮች እና ሰራተኞችን አቅም በመገንባት በተመደቡበት የስራ መደብ ላይ ውጤታማ በመሆን በአዲስ መንፈስና ተነሳሽነት የባለሥልጣኑን ተልዕኮ በብቃት ይወጡ ዘንድ አቅምን የሚገነባ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ሆኖ

**ወደ ገጽ 2 ዞራል!**

**ከገጽ 1 የዞረ..**

በመገኘቱ ነው ብለዋል ፡፡

አቶ ወንዳለ አክለውም በበጀት ዓመቱ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያቀዳቸውን ተግባራት በዉጤታማነት ለመፈፀም በተጠያቂነት መንፈስ ፣ በመደጋገፍና በመተባበር ተግባራትን በብቃት መፈፀም ተገቢ ስለሆነ ስልጠናውን በንቃት መከታተልና የስራ መመሪያ በማድረግ በቀጣይ ለስራ ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ሰልጣኞችን በማሳሰብ ስልጠናውን አስጀምረዋል ፡፡

በስልጠናው መድረኩ ላይ በቲም ቢዉልዲንግና ኢንተለጀንስ በባለስልጣኑ የእንስሳት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በዶ/ር ሀሚድ ጀማል ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በተመሳሳይ በእቅድና በጀት ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መሰረት አበባው የባለስልጣኑን የአስር ዓመት፣ የሶስት ዓመት እና የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለሰልጣኞች አቅርበዋል ፡፡

የስልጠናው ተሳታፊዎችም ስልጠናው ወቅቱን የጠበቀና ለስራቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን ገልፀው አገልግሎት አሰጣጥን ከማሻሻል ፣ ከቅንጅታዊ አሰራር እና የተመደበውን ሀብት በጋራና በአግባቡ ከመጠቀም አኳያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በተከታታይ መሰጠት እንዳለባቸው አሳስበው በተለይም ደግሞ እቅዶች በወቅቱ ለሰራተኛው ቀርበው መገምገም አለባቸውም ብለዋል። በተጨማሪም በስልጠናው ላይ ያገኙትን ግንዛቤ በማሳደግ ለአንድ ተቋማዊ ግንባታ ያላቸውን ትልቅ ሀላፊነት በመረዳት በተነሳሽነት መንፈስ በቅንጅት እንደሚሰሩ ገልፀዋል። በመጨረሻም የእፅዋት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንዳለ ሀብታሙ የተዘጋጀው ስልጠና የእርስ በእርስ መማማሪያና የተግባበት መድረክ እንደመሆኑ መጠን አቅምን በመገንባት

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከእንስሳት መድሀኒት አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች ጋር የምክክር መድረክ አካሄደ።





የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያ አስመጪ፤አከፋፋይ ና ላኪ ድርጅቶች ጋር በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱዩት የመሰብሰቢያ አዳራሽ የምክክር መድረክ አካሂደ። የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ የምክክር መድረኩ ዋና ዓላማ ከእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያ አስመጪ፤አከፋፋይ ና ላኪ ድርጅቶች ምርቶቻቸው ላይ ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነትን በማስጠበቅ በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እንዲያስችል ህግና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰሩ ግንዛቤን ለመፍጠር ያለመ ስለሆነ ቀልጣፋና ዘመናዊ አሰራር እንዲኖር ደንበኞቻችን የተዘጋጁ መመሪያዎችንና ህጎችን አውቀው በተግባር ላይ ማዋል እንደሚገባ አስገንዝበው የምክክር መድረኩን በይፋ ጀምረዋል።

የእንስሳት መድኃኒት ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ሰለሞን ከበደ ከእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያ አስመጪ፤አከፋፋይ ና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያን ለምክክር

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

PAGE 3

## የፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ምዝገባ በኦን ላይን ሲስተም ሊጀመር መሆኑ ተገለፀ።




የፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሪጉላቶሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር በየነ ልደቱ ለፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ተቋማት የብቃት ሰርተፍኬት ለመስጠት ፣ምዝገባ ለማካሄድ፣ ቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠትና የአስመጪዎችና አምራቾች ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት እንዲሁም ሌሎችን ስራዎች ለመስራት ለደንበኞች ኦንላይን ምዝገባ አገልግሎት በቅርቡ መሰጠት እንደሚጀምር ተናግረዋል።

ዶ/ር በየነ የኦን ላይን ሲስተም መዘርጋት ዋና ዓላማውም ዘመኑን የዋጀና ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት በተለይም እንደ ተቋም የሚነሱ የግልፅነት ችግሮችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚቀርፍ ነው ያሉ ሲሆን በተለይም በተገልጋይ አካላት ከጊዜ ጋር ተያይዞ የሚነሱትን እንግልቶች ለማስወገድ ወሳኝ መሆኑን ገልፀዋል። ተገልጋይ አካላት ለዘመናት ሲጠብቁት የነበረ የኦን ላይን ሲስተም ዝርጋታ በተለይም በፊት ሲስተናገዱበት ከነበረው ኋላ ቀር አሰራር ወጥተው ዘመኑን የዋጀና ቀልጣፋ የአሰራር ሲስተም በመፈጠሩና በተለይም ህገ ወጥ ስራዎች የሚከስምበት በመሆኑ እንዲሁም የአሰራር ሂደቱን ግልፅና ቀላል በማድረጉ በተገልጋዮቹ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳገኘም ዶ/ር በየነ አስረድተዋል። በዚህም መሰረት የኦን ላይን ምዝገባ ስርዓቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚጀመር በማመን በፍጥነት በታለመለትና በታሰበው ልክም ከግብ እንዲደርስ የባለሙያዎች ግንዛቤና ብቃት ወሳኝ በመሆኑ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ስልጠና መሰጠቱን ገልፀዋል።

በመጨረሻም ስራ አስፈፃሚው ተገልጋይ አካላት በዚህ በሚዘረጋው ሲስተም ብቻ መጠቀም እንዳለባቸውና ተጠያቂነትና ሀላፊነት የተሞላበትን የአሰራር ስርዓት መከተል እንደሚገባ በመግለፅ በተቋሙ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትም ሲስተሙ ቀጣይነት እንዲኖረው ከማድረግ አንፃር የራሳቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል። ጨምረውም የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ ተቋም በመሆኑ ሁሉም የስራ ክፍሎች ዘመናዊይና ግልፅ የአሰራር ስርዓትን መከተል ያስፈልጋል ብለዋል።

**ከገፅ 2 የዞረ**

ስራዎቻቸውን በብቃት መፈፀምና ተቋማችንን የማዘመን ስራ መስራት አለብን ብለዋል ። ጨምረውም በመድረኩ የተነሱ ሀሳቦች አስፈላጊና ለተሻለ ስራ የሚያነሳሱ መሆኑን በመግለፅ ለወደፊትም ችግር ፈቺና ተከታታይነት ያለው ስልጠና እንደሚሰጥ ገልፀው ባለሙያዎችም በተመደቡበት የስራ መስክ ላይ ሀላፊነታቸውን በሚገባ መወጣት እንዳለባቸው በማሳሰብ ለቀሩት ሰራተኞችም በቀጣይ ስልጠና እንደሚሰጥ ተናግረዋል ።

## የአንድ ተቋም ስራ ውጤታማ የሚሆነው ሁሉም በተመደበበት የስራ መስክ በትብብር መንፈስ በትጋት ሲሰራ ነው፡፡

**አቶ መሰሉ ዋጋው ጽ/ቤት ሀላፊ**



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በግብርና ዘርፉ የተጠናከረ ሬጉላቶሪ ስርዓት በመዘርጋትና በመተግበር በዓለም አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ በሰው፣ በእንስሳትና በእጽዋት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳትና ተጽዕኖ እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ የማስቻል ዓላማ ይዞ የፌደራል መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር በመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 45 ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት የተቋቋመ የፌደራል መ/ቤት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ይህንን ዓላማና ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ የህግ ማዕቀፎችን አካቶ መስራት፣ ሴቶች በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፣ የተቋሙ የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት የሚያረጋግጥ የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዕቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ፤አፈጻጸሙንም መከታተል፤ ለብልሹ አሰራር የሚዳርጉ የአሠራር ዘዴዎችን ለማስተካከል /ለመድፈን/ የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችና ስልቶች በማጥናት ለዋና ዳይሬክተሩ ማቅረብ፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱን የህዝብ ግንኙነትና ስርዐተ ተግባቦት (communication) ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፤ተልዕኮና አላማ/ግብ ጋር በተስማማ መንገድ ለመከወን የሚያስችል መርሃ ግብር መዘጋጀቱን የመከታተልና የማስተባበር ስራዎችን የሚሰሩት የባለስልጣኑ ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ መሰሉ ዋጋው በዚህ ወር የጋዜጣ እትማችን ላይ መረጃዎችን እያካፈሉን እንግዳችን ሆነው ቆይተዋል፡፡ መልካም ንባብ ፡፡

**ህዝብ ግንኙነት፡-** የባለስልጣኑ ፅ/ቤት ሀላፊ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው ?

**አቶ መሰሉ፡-** የጽ/ቤት ሀላፊ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሲሆን ጽ/ቤቱ በርካታ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ ከነዚህም መካከል በዓመታዊ ዕቅዱ ላይ በአፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሚያስፈልግ በጀትና ግብዓቶች የዕቅድ አካል ተደርገው መዘርዘራቸውን ያረጋግጣል፤ የባለሥልጣኑን የእለት ተእለት ተግባራት ለማከናወን ከተለያዩ የዋና እና ደጋፊ ሥራ ሂደቶች/ ስራ አስፈፃሚዎች/ እንዲሁም የተገልጋይ ጉዳዮችን ማስተናገጃ ሥርአት ይዘረጋል፣ በመስሪያ ቤቱ የሚወጡ አዋጆችን፤ደንቦች ፤ መመሪያዎች እና ስምምነቶች ከሀገሪቱ ህጎች ጋር የማይጋጩ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የህግ ማእቀፎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን ዝግጅት በማስተባበር ይመራል፣ የተቋሙን ተልዕኮ ከማሳካት አንጻር ችግሮችን በመለየት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል፣ ከኢትዮጵያ ግብርና ቁጥጥር ባለስልጣን ዓላማ አንጻር

ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት በመለየትና የስጋት ተጋላጭነት ያላቸውን በማስቀመጥ የስጋት ማምከኛ ስርአት አዘጋጅቶ ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፤ የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱን የህዝብ ግንኙነትና ስርዐተ ተግባቦት (communication) ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፤ተልዕኮና አላማ/ግብ ጋር በተስማማ መንገድ ለመከወን የሚያስችል መርሃ ግብር መዘጋጀቱን ይከታተላል፤ ተቋሙን የሚመለከቱ፤ በአገር ዓቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ ሁነቶችንና መድረኮችን (ሲምፓዚየሞች፣ኤግዚቢሽኖች፣ ኮንፍረንሶች፣ የምክክር መድረኮች ወዘተ) በቅድሚያ ለይቶ በዕቅድ እንዲያዙ በማድረግ መድረኮቹንም ለተቋማዊ የገጽታ ግንባታ ሥራ ጠቀሜታ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ የተቋሙ የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት የሚያረጋግጥ የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዕቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ፤አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ለብልሹ አሰራር የሚዳርጉ የአሠራር ዘዴዎችን ለማስተካከል /ለመድፈን/ የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችና ስልቶችን በማጥናት ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሴቶች፣ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፤ ከዚህ ባለፈም ሴት ሠራተኞችን ለማብቃትና በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ላይ እንዲመደቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በዝውውር፣ በድልድል፣ በትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ የአሰራር ስርአቶችን መተግበራቸውን ይከታተላል፤ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ በተለይም ወላጆቻቸውን ያጡና ተንከባካቢ የሌላቸው ሕጻናት ፍቅር፣ ክብካቤ፣ ድጋፍ እና ጥበቃ አግኝተውና መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ እንዲያድጉ በሴክተሩ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በባለስልጣኑ ምቹ የህጻናት ማቆያ እንዲኖር፤ አስፈላጊ መገልገያ ቁሳቁሶችና ተንከባካቢዎች እንዲሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ ተፈጻሚነቱንም ይቆጣጠራል፤ በበላይ አመራሩ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ከህግና መ/ቤቱ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር በመለየት በማስረጃ ተደግፎ እንዲቀርብ በማድረግ፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ለአመራሩ ያቀርባል፣ ከዚህ ባለፈም የበላይ አመራሩ ለሚካፈሉባቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች የሚያስፈለጉ መረጃዎችንና መግለጫዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ተጠናቅረው እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት እንዲሻሻል አህጉራዊና አለማቀፋዊ ልምዶችና ነባራዊ እውነታዎች ተዳሰው የሚቀመሩበትንና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ያስፋፋል። የባለስልጣኑ ተልዕኮ ውጤታማ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የውስጥና የውጭ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ውጤታማ ስራ ይሰራል፤ በተጨማሪም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከመንግሥት፣ ከፕሬስ፣

ከገፅ 5 የዞረ

ተሞክሮዎችን ይቀምራል፣ ያስፋፋል። የባለስልጣኑ ተልዕኮ ውጤታማ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የውስጥና የውጭ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ውጤታማ ስራ ይሰራል፤ በተጨማሪም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከመንግሥት፣ ከፕሬስ፣ ከባለድርሻ አካላት፤ ከተገልጋዮች እና ከማኅበረሰብ ጋር ያለውን የግኙነት በመከታተል፤ ውጤቱንም ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፤ የዕቅድና ፕሮግራም ክንውን እና አጠቃላይ የበጀት አጠቃቀምን አስመልክቶ አፈጻጸሙን በጋራ ገምግሞ፣ አፈጻጸሙንም ያረጋግጣል፤ እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለሚቀርቡ ጥቆማዎችና ቅሬታዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በማቅረብ፤ ወቅታዊና ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጥበት በማድረግ አፈፃጸሙን ይከታተላል፤ ጽ/ቤቱን አስመልክቶ በየጊዜው ለበላይ አካላትና ለተለያዩ መ/ቤቶች የሚቀርቡ ዕቅዶችና ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው መቅረባቸውን በመከታተል፣ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፤ በባለስልጣን መ/ቤቱና በባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የፕሮቶኮል ስምምነት ሰነዶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፣ የባለስልጣን መ/ቤቱ ስራ ማስፈጸሚያ መመሪያዎችና ስምምነቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል እንዲሁም በሥራ ክፍሉ ውስጥ ጠንካራ የስራ ባህልና ተነሳሽነት እንዲፈጠርና በዘላቂነት እንዲቀጥል ተገቢውን አመራር በመስጠት የክፍሉን ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም በየምዕራፉ ይገመግማል፣ የተጠቃለለ የምዘና ሪፖርቶችን ያቀርባል ማለት ነው።

**ህዝብ ግንኙነት፦** ባለስልጣን መ/ቤቱ የህግ ማዕቀፎችን አካቶ ከመስራት አኳያ ያለው አሰራር ምን ይመስላል ?

**አቶ መሰሉ፦** የባለስልጣኑ ሥራዎች በሕግ አግባብ እንዲሰሩ ግብ ተይዞ የህግ ረቂቅ ማዘጋጀት፣ የህግ ረቂቅ ማጸደቅ፣ የህግ ግንዛቤ ማሰደግ፣ ውጤታማ የህግ አፈጻጸም፣ ውጤታማ የህግ ድጋፍ፤ ግምገማና ክትትል፣ እየተሰራ ይገኛል። የባለስልጣኑን የህግ ማዕቀፍ ፍላጎቶችን እና ክፈተቶችን በመለየት ከተለያዩ ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመቀናጀት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አስፈጻሚ የህግ ድጋፍ እንዲደርግ እገዛ እያደረገ ይገኛል። በዚህም መሰረት 2 አዋጅ፣ 1 ደንብ እና 3 መመሪያ ለማጸደቅ በእቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል።

**ህዝብ ግንኙነት፦** የተቋሙን ተልዕኮ ከማሳካትና ችግሮችን ከመለየት እንዲሁም መፍትሔ እንዲያገኙ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አኳያ እየሰራ ያለው ስራ ምን ይመስላል?

**አቶ መሰሉ፦** የተቋሙ ተልዕኮ የአካባቢን ደህነነት በማስጠበቅ የግብርና ምርት፤ ግብዓት፣ ቴክኖሎጂ የግብርና ኤክስቴንሽን አገለግሎት ጥራት፣ ደህንነት፣ ጤናማነት እና ፍቱንነት ማረጋገጥ፣ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ገበያን ለማሻሻል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓትን በመገንባት ለአገሪቱ የሚበጀውን ጥቅም ማስጠበቅ ስለሆነ ከሚመለከታቸው ስራ አስፈጻሚዎች ሲረቀቅ ከህግ አገልግሎት ስራ ጋር በመሆን ችግሮች እየተለዩ በስራ አመራር ማናጅመንት ውሳኔ እየተሰጠባቸው የተፈቱ ብዙ ናቸው። ለምሳሌ የማዕከላትና የጣቢያ ኃላፊዎች ምደባ፤ ምደባ ያላገኙ ሰራተኞች እንዲመደቡ፣

**ወደ ገጽ 7 ይዞራል!**



## ከገፅ5 የዞረ

የተቋሙን ሀብት በአግባብ መጠቀም ለምሳሌ የነዳጅና የተሽከርካሪ አጠቃቀም፤ የእንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት አሰጣጥ የመሳሰሉት ችግሮች መፍትሄ እንዲሰጣቸው ተደርጓል።

**ህዝብ ግንኙነት፡-** በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚፈጠሩ ህግ -ጥሰቶችንና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከልና በተለይም ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የአሰራር ሂደቶችን ወደ ግልፅና ተጠያቂነት ከማምጣት አኳያ ምን እየተሰራ ነው ?

**አቶ መሰሉ፡-** በባለስልጣን መ/ቤቱ የሥነ ምግባር ደንቦች እና የፀረ ሙስና ሕጎች በማክበር ከሙስና የፀዳ አሰራርና መልካም አስተዳዳር እንዲሰፍን ግብ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል። ይህን ለማሳካት በ3 ቁልፍ ውጤት አመልካች ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል። በዚህም መሰረት የሥነ ምግባር የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መቀነስ እና የሙስና መረጃ አስተዳዳር ውጤታማነትን የማረጋገጥ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

PAGE 7

**ህዝብ ግንኙነት፡-** የተቋሙ ተልዕኮ ውጤታማ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የውስጥና የውጭ አካላት ጋር ተናቦ ከመስራት አኳያ ያለው ሚና ምን ይመስላል?

**አቶ መሰሉ፡-** የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት ከባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል። ውይይት መድረኩ ቀጣይ መሆን ስላለበት ላኪና ተቀባይአገራትን፣ ባለድርሻ አካላትንና ተገልገዮችን በመለየት የተቋሙን ራዕይ፤ ተልዕኮ እና የአሰራር የህግ ማዕቀፍ ማስተዋወቅ ቅድሚያ ሚሰጠው ስራ ነው። በመሆኑም ወደ ኢትዮጵያ ላኪ አገራት ቁጥር 45 እና ከኢትዮጵያ ተቀባይ አገራት ቁጥር 28 አገሮች እንደሆኑ ተለይተዋል። ከተገልጋዮች አንጻር ሲታይ አምራች 105፣ ላኪ 150 እና አስመጭ 249 ተቋማት ተለይተዋል። ከእነዚህ በተጨማሪ ለተቋሙ ስራ ጉልህ ድርሻ ያላቸው 32 ዋና ባለድርሻ አካላት፣ 14 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ 12 የሙያ ማህበራትና 2 አገልግሎት ሰጭ ደርጅቶች ተለይተዋል። ከእነዚህ ድርችቶች ጋር የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት በሂደት ላይ እንገኛለን።

**ህዝብ ግንኙነት፡-** ጽ/ቤቱ በስሩ ለሚገኙ ስራ አስፈፃሚዎች ድጋፍና ክትትል ከማድረግ አኳያ ያለው የስራ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

**አቶ መሰሉ፡-** በፅ/ቤት ስር ያሉ ስራ አስፈጻሚዎች የበጀት አመቱ እቅድ ቁልፍ ውጤት አመልካች እቅድ መሰረት ተደርጎ እንዲታቀድ መነሻ ሀሳብ በጽሁፍ የመስጠት ስራ ተሰርቷል።

## ከገጽ 7 የዞረ!

በስራ አስፈጻሚዎች የታቀደው እቅድ በስትራቴጅክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አስተያይት እንዲሰጥበት በማድረግ በጋር በመገምገም ጸድቆ ወደ ስራ እንዲገባ ሆኖል። አፈጻጸሙም በ1ኛው እና በ2ኛው ሩብ ዓመት ከስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመገምገም ለቀጣይ አቅጣጫ አስቀምጠናል። ስራ አስፈጻሚዎች የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ያልተማከለ አሰራር እንዲከተሉ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። ከሌሎች ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በቅንጅት ስራ ለመስራት የጽ/ቤት ኃላፊውን እገዛ በሚጠይቁ ስራዎች ላይ ድጋፍ እየተሰጠ ይገኛል።

**ህዝብ ግንኙነት፡-** በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ?

**አቶ መሰሉ፡-** የአንድ ተቋም ስራ ውጤታማ የሚሆነው ሁሉም በተመደበበት ስራ በትብብር መንፈስ በትጋት ሲሰራ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም ሁላችንም ከአድሎአዊ አሰራር ነጻ በመሆን፤ ብልሹ አሰራርን በመጸየፍና ሀብትን በቁጠባ በመጠቀም ለውጤት እንስራ።

**ህዝብ ግንኙነት፡-** ስነበረን ቆይታ ከልብ አመሰግናለሁ።

### ከገፅ 8 የዞረ

የተሰጡ ሲሆን በተለይ ምላሽ ያስፈልጋቸዋል ለተባሉ ጥያቄዎች በገለፃ አቅራቢዎች ምላሽ ከተሰጠ በኋላ ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ከተሳታፊዎች የተነሱ ገንቢ ሃሳቦችን በግብዓትነት በመውሰድ የቀጣይ ስራችን አካል አድርገን የምንሰራቸው መሆኑን በመግለፅ የተቋማችንን የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያ አስመጪ፤አከፋፋይ ና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያን ማወቅና በተግባር ላይ በማዋል የበኩላችሁን ኃላፊነት መወጣጥ ይገባል በማለት የውይይት መድረኩ ተጠናቋል።

### ከገፅ 2 የዞረ

መድረክ ተሳታፊዎች ያቀረቡ ሲሆን በዚህ ህግ እና መመሪያና መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያ አስመጪ፤አከፋፋይ ና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ውጪ ማስተናገድ እንደማይቻል አውቀው ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ አብራርተዋል። በተለይም አገር ውስጥ ለሚሸጡና ለሚያከፋፍሉ ድርጅቶች የአከመቻቸት ሂደት የሙቀትና የቅዝቃዜ መጠኑን መለኪያ ቴርሞ ሜትር ፣ መድኃኒቱ የተሰራበትንና የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገለፅ ፅሑፍ መኖሩን፤ የሚወገዱ መድኃኒቶች አከመቻቸት እንዲሁም ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ ህግና መመሪያውን ተከትለው መስራት እንዳለባቸው አስረድተው ከህግና መመሪያው ውጪ ለሚሰሩ ድርጅቶችና ባለሙያዎች የቃልና የፅሑፍ ማስጠንቀቂ፣ የእገዳ እንዲሁም የስረዛ ቅጣቶች እንደሚጣልባቸው አብራርተዋል፡፤

የእንስሳት ሪጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሀሚድ ጀማል በበኩላቸው ባለፉት የምክክር መድረረኮች ላይ ጥሩ ግንዛቤ የተወሰደበትና ተነሳሽነትን የፈጠረ መሆኑን ገልፀው በአሁኑ መድረክም በተሻለ ሆኔታ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስችል መሆኑን በመግለፅ በተለይም በመስክ በተገኘው ግኝት መሰረትበመድኃኒት አያያዝና አቀማመጥ ላይ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስበው ለስራ ማነቆ የሆኑና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸውን ህግና መመሪያዎችንም ወስደን በማስተካከል የጋራ ተግባቦትን በመፍጠር ለቀጣይ ስራ ውጤታማነት በትኩረት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

በመጨረሻም የቀረቡ ገለፃዎችን መሰረት በማድረግ በመድረኩ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

# ቡሬ ኢትዮጵያ



ምርጥና አስተማሪ አባባሎች

በአንድ ጫካ ውስጥ መልካቸው ነጭ፣ ጥቁር እና ግንባሩ ቦቃ የሆኑ ሶስት በሬዎች ይኖሩ ነበር። አንበሳን ጨምሮ የትኛውም አውሬ ቢመጣ ክብ በመሥራት እየተዋጉ አላስጠጋ አሉ።

....አንድ ቀን ግን አያ ጅቦ መጣና “ይሔ ነጭ በሬ ያስጨርሳችኋል፤ እሱ ባይኖር በጨለማ አትታዩም” የሚል መጥፎ ሀሳብ በውስጣቸው ለቀቀባቸው። ሁለቱ በሬዎች ተባብረው ነጩን በሬ አባረሩት። ጅቡም ብቻውን አግኝቶት ነጩን በሬ በላው።

ጅቡ ሌላ ጊዜ ተመለሰና ለጥቁሩ በሬ “ግንባረ ቦቃው ካለ አሁንም ለአደጋ የተጋለጥህ ነህ” አለው። በዚህ የተነሳ ሁለቱ በሬዎች ተለያዩ። ጅቡም ግንባረ ቦቃውን በላው።

በሌላ ቀን ጅቡ ጥቁር በሬው ጋር ሄደ። በሬውም “ዛሬ ምን ፈልገህ መጣህ? ልትበላኝ ነው?” አለው። ጅቡም “አንተ እኮ የተበላከው መጀመሪያ ጓደኞችህን አሳልፈህ የሰጠህ ጊዜ ነው” ብሎ ጥቁሩን በሬ በላው።

ልብ ብለን ልንረዳው የሚገባው ነገር ሁሌም ልዩነታችን ውበትና ጥንካሬ የሚኖረው በአንድነታችን ውስጥ ነው!

አንድ ስንሆን እንቆማለን፤ ስንከፋፈል እንወድቃለን!

ከታላላቅ ሰዎች ዓባባል

❖በብርሃን ስትሆን ሁሉ ነገር ይከተልሃል:: ጨለማ ውስጥ ከሆንክ ግን ጥላህ እንኳን አይከተልህም # ሂትለር

❖ሳንቲም ብዙ ድምፅ ያሰማል። ገንዘብ ግን ምንም አያሰማም። ስለዚህ ዋጋህ ሲጨምር ወሬህን እየቀነስክ ና! #ሼክስፒር




